ኢ ዴ አ ፓ - መ ድ ኅ ን
UEDP - MEDHIN
Head Office ☐ Branch Office ☐ Support Group ☐

ቀን 5/10/2001 ዓ.ም
Date
ቁጥር ኢ.መ 103/2001
Ref.

## ከኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) የተሰጠ መግለጫ
## መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ የሚባለውን ስብስብ አቋም ይዘን ልንታገለው ወስነናል!

ፓርቲያችን ኢዴፓ ተመስርቶ የአገሪቱን የፖለቲካ መድረክ ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በበጐ አይን ሲያዩት አልምደዱም። በአንድ በኩል ፓርቲያችን ኢዴፓ በገዥው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚው ጐራ ውስጥም የሚታዩ የአመለካከትና የአሠራር ድክመቶችን ጭምር እታገላለሁ በማለት ግልፅ አቋም ይዞ በመምጣቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአብዛኛው በአዲሱ ትውልድ አባላት የተገነባው ኢዴፓ የሚያደርገውን የጐላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሌሎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በእነሱ ህልውና ላይ የመጣ አደጋ እንደሆነ አድርገው በማዩታቸው የተለያዩ ስልት በመጠቀም ሲያዳክሙት ሲሞክሩ ታይተዋል።

በተለይም ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችን ፖለቲካ በተፈጠረው ችግር እነዚህ ኃይሎች ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነና የተቀነባበረ የስሉባልታ ዘመቻ በኢዴፓ ላይ በመክፈት የፓርቲውን አመራር አባላት ስም የሚያጠፉ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ በተሳሳተ አሉባልታ ተነሳስቶ ህይምታቸውን ጭምር እንዲያጠፋቸው የሚያስችል ሙከራ አድርገው በህዝቡ ጨዋነት ጥረታቸው ሳይሳካ ቀርቷል። ኢዴፓ የተካሄደበትን የአሉባልታ ዘመቻ ተቋቁሞ ፓርላማ ገብቶ እንደገና ማንሰራራትና የህዝቡን ቀልብ መሳብ ሲጀምርም እነዚህ ኃይሎች ስልታቸውን በመቀዩር ኢዴፓን ከኢህአዴግ ጋር ልዩ ግንኙነት ያለው ፓርቲ አስመስሎ ለህዝቡ ለማቅረብ የሚያስችላቸውን ጥረት አድርገዋል።

ይኸውም በፓርላማው ውስጥ በአጀንዳ የሚቀርቡ አገርንና ህዝብን የሚጠቅሙ አጀንዳዎችን ሳይቀር ከኢዴፓ በተፃራሪ በጭፍን በመቃወም፣ በፓርላማው ውስጥ በወር አንድ ጊዜ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄ ለማቅረብና በተቃዋሚዎች ቀን አጀንዳ ለማቅረብ

Head Office ☎ 50 87 27 ✆ 50 87 30 ✉ 101458
Addis Ababa 50 87 28 E-mail:addisedepa@hotmail.com
Our Account No. Addis Ababa, Bank of Abyssinia Filwuha Branch A/C 145
Branch Office or Support Group in ____ Tel: ____ Fax: ____ P.O.Box: ____

ያላቸውን መብት ሆን ብለው ባለመጠቀም ኢዴፓ በፓርላማው ውስጥ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄዎች የሚያቀርበውና በተቃዋሚዎች ቀን አጀንዳ የሚያስይዘው በተለዩ ሁኔታ በኢህአዴግ ውለታ እየተደረገለት እንደሆነ አስመስለው በማቅረብ ህዝቡ የተዛባ አመለካከት በኢዴፓ ላይ እንዲኖረው ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። የተለያዩ ፓርቲዎች እንዲወያዩበትና እንዲከራከሩበት ተብሎ "መድረክ" በሚል ስያሜ አንድ የምሽት ፕሮግራም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከዓመት በፊት ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች በማንኛውም የውይይትም ሆነ የክርክር መድረክ ላይ ከኢዴፓ ጋር አብረን አንቀርብም በማለታቸው ምክኒያት ፕሮግራሙ እንዲቋረጥና ዕድሉን እንድናጣው ተደርጓል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ኢዴፓን ለማሳጣት የሚያስችላቸው መስሎ ስለታያቸው ብቻ እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች በፓርላማ ውስጥ ባሉ ፓርቲዎች መካከል ሲደረግ ከነበረው የድርድር መድረክ ያለ በቂ ምክኒያት እረግጠው በመውጣታቸው የተቃዋሚውን ጎራ በብዙ መልኩ ሊጠቅም ይችል የነበረው የፓርቲዎች የድርድር መድረክ ሊቋረጥ ችሏል። ይህ ሁሉ አልበቃቸው ብሎ ሰሞኑን በአዲስ አበባና በሃዋሣ ከተሞች ኢዴፓ በአካሄዳቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይም የመድረኩ አባል የሆነው አንድነት ፓርቲ አባሉቹን አደራጅቶ በማስገባት ህዝባዊ ስብሰባዎቹን ለመበጥበጥና ለመበተን ያደረገው ሙከራ ሳይሳካለት ቀርቷል። ይህንንም የራሱ የአንድነት ፓርቲ አባላት የሆኑ ወጣቶች በፈፀሙት ድርጊት በመፀፀት ማን እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት እንዲፈፅሙ እንዳሰማራቸው ቢሯችን ድረስ መጥተው አጋልጠዋል።

እነዚህ ምንም ዓይነት የጋራ አገራዊ አጀንዳ በመካከላቸው ሳይኖር ለሥርዓቱ ገደብ የለሽ ጥላቻ ስላላቸው ብቻ የተሰባሰቡና ትናንት በተለያዩ ጉራዎች ተሰልፈው እርስ በርስ በጠላትነት ሲተያዩ የነበሩ ድርጅቶች ይህንን ሁሉ ደባ መፈፀማቸው አልበቃቸው ብሎ በየኤምባሲው ቢሮ እዩዞሩ "ከእንግዲህ ለማንኛውም ዓይነት ግብዣም ሆነ ውይይት ከኢዴፓ ጋር ከጋበዛችሁን ልንገኝ አንችልም" በማለት ኢዴፓ በውጭ ዲፕሎማቶች እንዲገለል ለማድረግ ጥረት አድርገዋል። እንዲህ ዓይነቱ በፕሮፌሰር በዬነ ጴጥሮስ አስተባባሪነት የተካሄደው ዘመቻም ለአሠራራቸው ችግር እንደፈጠረባቸው በርካታ የውጭ ዲፕሎማቶች ለኢዴፓ አመራሮች በግልፅ ያሳወቁ ሲሆን፣ በቅርቡ ከአዲሱ የአሜሪካ የአባማ አስተዳደር መጥተው የነበሩት የሴኔት አባልም ሁሉንም

ተቃዋሚዎች በአንድ ላይ አግኝተው ሲያነጋግሩ ኢዴፓ ሳይጋበዝ የቀረው በዚሁ እነ ፕሮፌሰር በዩነ ባቀረቡት ቅድመ-ሁኔታ ምክኒያት እንደሆነ የአሜሪካው አምባሳደር ዶናልድ ያማሚቶ በቅርቡ ለፓርቲያችን ፕሬዘዳንት ለአቶ ልደቱ አያሌው ገልፀውላቸዋል።

በአሁኑ ወቅት የኢዴፓ እንቅስቃሴ እያደገ መምጣቱ እያሳሰባቸው የመጣው እነዚህ ኃይሎች በፓርቲያችን ላይ ያላቸው ጥላቻ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያሳይ ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነ ድርጊት ሰሞኑን በገሃድ ሲፈፅሙ በመታዬታቸውም ፓርቲያችን ይህንን መግለጫ ሊያወጣና ከእንግዲህም እነዚህን ኃይሎች በተመለከተ ግልፅ አቋም ይዞ ሊታገላቸው ተገዷል። ይኸውም ሰሞኑን በአገራችን የስራ ጉብኝት ላይ ከሚገኙት ከኔዘርላንድስ የሰብዓዊ መብት አምባሳደር ከሚ/ር አርጃን ሃምበርገር ጋር የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች እንዲገናኙ የኔዘርላንድስ ኤምባሲ አንድ ፕሮግራም በኤምባሲው ጽህፈት ቤት ውስጥ አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ስብሰባ ከልዑካን ቡድኑ ጋር እንዲገናኙና ስለመጭው የአገራችን ብሔራዊ ምርጫ እንዲወያዩ ተጋብዘው የነበሩት ኢህአዴግ፣ ኢዴፓና መድረኩ ነበሩ። ነገር ግን በኋላ ላይ የመድረኩ አመራሮች "ከኢህአዴግ ጋር በአንድ ጠረንጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን መወያዬት አንፈልግም" የሚል ቅድመ-ሁኔታ በማቅረባቸው ኢዴፓና መድረኩ ብቻ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ጥሪ ተላለፈ።

በተደረገው ጥሪ መሠረት እሮብ ሰኔ 3 ቀን 2001 ዓ.ም ከጧቱ ሦስት ሰዓት ላይ የፓርቲዎቹ ተወካዮች በኤምባሲው ጽህፈት ቤት ተገኝተው ከልዑካን ቡድኑ ጋር ስብሰባ ሲጀመር መድረኩን ወክለው ከተገኙት ሰዎች ውስጥ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ ገብሩ አስራት የስነ-ሥርዓት ጥያቄ አለን በማለት "ኢዴፓ በዚህ ስብሰባ ላይ የሚሳተፍ ከሆነ እኛ በውይይቱ የመቀጠል ፍላጐት የለንም" የሚል ቅድመ-ሁኔታ አቀረቡ። የልዑካን ቡድኑ አባላት በተከሰተው ነገር ተደናግጠው "ስለመጭው ምርጫ ከማንም ጋር ለመወያዬት ምን የሚያስፈራ ነገር አለ? ፓርላማ ውስጥስ አንድ ላይ እየተሰበሰባችሁ ትሰሩ የለም ወይ? እንደዚህ እያላችሁስ ዴሞክራሲን በአገራችሁ እንዴት ልትገነቡ ትችላላችሁ? ሁላችሁንም በተናጠል ለማነጋገር እኛ ጊዜውም የለንም። እባካችሁ እንዲህ ዓይነቱን ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ተውትና ውይይቱ ይጀመር" በማለት ቢማፀኑም የመድረኩ መሪዎች "በምንም ዓይነት ከኢዴፓ ጋር ተቀምጠን

ውይይት ለማድረግ አንችልም" በማለት ስብሰባውን እረግጠው ለመውጣት ከመቀመጫቸው ተነሱ።

በምቅቱ ለአገር ክብር ሲባል ከውጭ ለመጡት ልዑካን ተገቢውን አክብሮት ማሳዬትና ፕሮግራማቸውም እንዳይበላሽ ማድረግ ተገቢ መስሎ የታያቸው የኢዴፓ ተምካይ "ፕሮግራማችሁ ከሚበላሽ እኔ ከስብሰባው ብወጣ ይሻላል። እናንተ ስብሰባችሁን ቀጥሉ" በማለት ስብሰባውን ለቀው በመውጣታቸው የልዑካን ቡድኑ አባላት ከመድረክ መሪዎች ጋር ውይይታቸውን ማካሄድ ችለዋል። ከእነሱ ጋር የተካሄደው ውይይት እንዳበቃም የልዑካን ቡድኑ ሌላ ቀጣይ ፕሮግራማቸውን በመሰረዝ ከኢዴፓ ተምካይ ጋር ሰፊ ውይይት አድርገዋል። የመድረክ መሪዎች ባሳዩት ተገቢ ያልሆነ ባህሪ እጅግ በማዘንም የልዑካን ቡድኑ አባላትና በኢትዮጵያ የኔዘርላንድስ አምባሳደር የኢዴፓን ተምካይ ስለተፈጠረው ችግር ይቅርታ ጠይቀዋል።

ኢዴፓ እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች ምንአልባት ወደፊት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ሊመጡ ይችላሉ ብሎ በማሰብ የሚፈፅሙትን ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነ ድርጊት ሁሉ ታግሶ እስከዛሬ ቆይቷል። ከእዚህ በኋላ ግን እንዲህ ዓይነቱን በህዝብ ትግል ስም የሚፈፀም ደባ በዝምታ ማለፍ ተገቢ ሆኖ አላገኘውም። እነዚህ መድረክ በሚል ስብስብ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች ለሥርዓቱ ካላቸው ገደብ የለሽ ጥላቻ በስተቀር በመካከላቸው ምንም ዓይነት የጋራ አጀንዳ የሌላቸው ከመሆኑም በላይ በየሂደቱ እያራመዱት የሚገኘው አቋምም የዴሞክራሲና የሃሣብ ነፃነት መኖርን በእጅጉ የሚፃረር ነው። የእነዚህን ኃይሎች ፀረ-ዴሞክራሲ አቋም ለረዥም ጊዜ ሲከታተል ቆይቶ ፓርቲያችን ዛሬ ላይ የደረሰበት ድምዳሜ እነዚህ ኃይሎች ነገ በሆነ መጥፎ የታሪክ አጋጣሚ የመንግሥት ሥልጣን በእጃቸው ቢገባ በአገራችን በአሁኑ ወቅት በአንፃራዊነት የሚታዬው ሃሣብን የመግለፅም ሆነ የመደራጀት ነፃነት ጭራሽ ደብዛው የሚጠፋ መሆኑን ነው።

ዛሬ እንደነሱ ተቃዋሚ ፓርቲ በሆነው ኢዴፓ ላይ እንዲህ ዓይነት የአፈና ድርጊት ለመፈፀም ሲሞክሩ የሚታዩ እነዚህ ኃይሎች ነገ ሁሉን ነገር ለማድረግ የሚያስችል የመንግሥት ሥልጣን በእጃቸው ውስጥ ቢገባ የሃሣብ ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ ከማፈንና ከማጥፋት ወደኋላ እንደማይመለሱ ከወዲሁ እርግጠኛ መሆን ይቻላል። በእርግጥም በመድረኩ ውስጥ ከሚገኙት ሰዎች ውስጥ አንዳንዶቹ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት የነበሩና ለአገር ጥቅም ሲባል በተፈጠረ ልዩነት ሳይሆን በራሳቸው ፓርቲ

ውስጥ የሚካሄድ የለውጥ ተሃድሶን በመቃወም በውስጠ ፓርቲ ትግል ተሸናፊ ሆነው የወጡ ሰዎች መሆናቸው ሲታይ፤ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹም "ጦርነትን መዋጋት ብቻ ሳይሆን መስራት እንችላለን" እያሉ በጦረኛ ባህሪያቸው በመኩራራት በህዝብ ላይ ሲመፃደቁ የነበሩና አንዳንዶቹም የትግራይ ርዕስ ብሄር በነበሩበት ወቅት በክልላቸው ተቃዋሚዎች እንዳይንቀሳቀሱ ሲያፍኑና የትግራይ ህዝብ ጋዜጣ ማንበብ እንኳ እንዳይችል አፈና ሲፈፅሙ የነበሩ መሆኑ ሲታይ፣ አንዳንዶቹም በሌላ የተለዩ ምክኒያት ሳይሆን የኢህአዴግ ባለሥልጣንና የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር በመሆን የሥልጣን ዘመናቸውን አሟጠው ከተጠቀሙ በኋላ "የኦሮሞ ህዝብ የመገንጠል መብቱን በህዝበ-ውሳኔ ሊያረጋግጥ ይገባል" በማለት የአክራሪነት አቋም ይዘው ከኢህአዴግ የተነጠሉ ሰዎች መሆናቸው ሲታይ፣በአጠቃላይም እነዚህ ሰዎች በሥርዓቱ ውስጥ ሆነው ለዓመታት አፈና ሲፈፅሙብን የኖሩ ሰዎች መሆናቸው ሲታይ ዛሬ መልካቸውን ቀይረው በተቃዋሚነት ስም ተደራጅተው በመምጣት ተመሳሳይ አፈና በኢዴፓ ላይ ለመፈፀም ሲሞክሩ ቢታይ ድሮውንም አምባገነንነት መታወቂያ ባህሪያቸው ነውና እምብዛም የሚያስደንቅ አይሆንም። ከእነዚህ ሰዎች ጋር በመሆን መድረክን ያቋቋሙት ሌሎቹ ግለሰቦችም ከአሁን በፊት በተለያዩ አምባገነናዊ ሥርዓቶችና የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ አባል ሆነው ተመሳሳይ አፈና በመፈፀም የሚታወቁ በመሆናቸው ዛሬ እንዲህ ዓይነቱን የማያዛልቅ ጥምረት ከቀድሞ የፖለቲካ ባላንጣዎቻቸው ጋር ፈጥረው ለተመሳሳይ ዓላማ ቢሰለፉ በእርግጥም የሚያስደንቅ አይደለም።

የሆነ ሆኖ እንደዚህ ዓይነቱ ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነ ስብስብ በተቃዋሚነት ስም ህዝብን አጭበርብሮ እንደገና ወደ ሥልጣን ሊቆናጠጥ የሚችልበት ዕድል ካገኘ አገራችንን ወደ ከፋ አደጋ የሚከት መሆኑ የማያጠራጥር ስለሆነ ኢዴፓ ይህ ኃይል ወደ ትክክለኛው መስመር እስካልገባ ድረስ አቅምና ሁኔታ በፈቀደለት መጠን አቋም ይዞ በፅናት እንደሚታገለው ያሳውቃል። ህዝቡም የዚህን ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነ ኃይል እውነተኛ ማንነት በውል ተረድቶ እንዲታገለው ኢዴፓ በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል።

የኢዴፓ ስራ-አስፈፃሚ ኮሚቴ
ሰኔ 5 ቀን 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢዴፓ የወደፊቱ ፓርቲ!